# የተረሳው ጋዜጠኛ

(ከ-ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን)

www.ethiopiansemay.blogspot.com

በወርሃ መስከረም 2005 ዓ.ም የመጀመሪያ ሳምንት የአውራምባ ታይምስ ድረ-ገፅ ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደ በመቆጨት ሥሜት የከተበውን ፅሁፍ አስነብቦን ነበር፡፡ "አድሎአዊው ይቅርታ እና አሣፋሪው የነጭ አምልኮ" በሚል ርዕሥ ለንባብ ያበቃው ያ ፅሁፍ በውስጡ መራር ቁጭት ያጋተ፣ ሞጋችና ሸንቋጭ ይዘት ነበረው፡፡

በእርግጥም ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ በወቅቱ ያነጣጠረበት ጉዳይ በእጅጉ የሚያስቆጭና ኢትዮጵያዊ ማንነትን የሚያጠይቅ… ወዘተ ነበር፡፡ እነሆ እኔም ከወራት በኋላ ያንኑ ጉዳይ አፅንኦት ሰጥቼ፣ ጥቂት ነገር ለማለት ወደድኩ፡፡ ብዘገይም "ጨርሶ ከመቅረት" ይሻላል በሚል፡፡ ግን ለምን ዘገየሁ? ብል ሰበብ አላጣም፡፡ ከሰበቦቹ አንዱ ተስፈኛ መሆኔ ሊሆን ይችላል፡፡ በጊዜ ወይም በቀናት ለውጥ የሚመጣ ነገር ሊኖር ይችላል በሚል ይሆናል፡፡ ታጋሽ መሆን አምሮኝም ሊሆን ይችላል፡፡ ያም ሆነ ይህ ሁሉም ሰበቦቼ አልሰመሩልኝም፡፡ እንኳን ሊሰምሩ የሚሰምሩም አይመስሉም፡፡ ስለዚህ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ በቁጭት ያወሳውን ጉዳይ በጥቂቱ፣ ከጥቂትም ጥቂት ለየት ባለ መልኩ ላነጣጥርበት ሻትኩ፡፡ ከሁሉ አስቀድሜ ጉዳዩን በምልሰት ላስታውስ፡፡

**ምልሰት**

ፀለምተኛው ክረምት (2004 ዓ.ም) ከመግባቱ አስቀድሞ ነበር በሽብርተኝነት ወንጀል ተከሰው የተፈረደባቸው፣ ነገር ግን ይቅርታ እንዲደረግላቸው  የጠየቁ እስረኞች አዲሱ ዓመት (2005 ዓ.ም) ሲጠባ እንደሚፈቱ የተሰማው፡፡ ያኔ የዜናውን እውን መሆን ብዙዎቻችን በተስፋ ጠብቀን ነበር፡፡ በተለይ የታሳሪዎቹ ቤተሰቦች የመስከረምን መጥባት በተስፋና በጉጉት ነበር የጠበቁት፡፡ ግን ምን ያደርጋል!? በተስፋ የተጠበቀው መስከረም ተስፋቸውን አጨንግፎ ነበር የመጣው፡፡

መንግስት በሽብርተኝነት ክስ ተከሰው ከተፈረደባቸውና ይቅርታ እንደጠየቁ ከተነገረላቸው እስረኞች መሃል ስዊድናዊ ዜግነት ያላቸውን (ጋዜጠኛ ማርቲን ስቲቨን እና ጆአን ስፔንሰርን) ብቻ ፈታ፡፡ ኢትዮጵያኖቹን ይቅርታ ጠያቂዎች ግን እዚያው የእስር ቤት በር እንደቀረቀረባቸው ተዋቸው፡፡ የአውራምባ ታይምስ ድረ-ገፅ ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደ ይህንን "ልዩ" ይቅርታዊ ይሁንታ ነው "አሣፋሪ" እና "የነጭ አምልኮ" ሲል አምርሮ የነቀፈው፡፡ በሌላ አገላለፅ ዳዊት ከበደ "መድሎ እና ማግለል ይቁም!" ሲል ነው መንግስትን የተቸው፡፡ እኔም አጠንክሬ የምለው ይህንኑ ነው፡፡ ግን….

**መድሎ ይቁም!?**

"መድሎ እና ማግለል ይቁም!" ይሉት ብሒል እንደ መርህም ይሁን እንደ መፈክር (አዲስ ግኝት ይመስል) ገንኖ መነገርና መደመጥ የተያዘው ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከተከሰተ በኋላ ይመስለኛል፡፡ ቫይረሱ ከሚያደርሰው ጉዳትና ከበሽታው መድኃኒት አልባነት በላይ፣ የሰው ልጆችን ክፉኛ ያጠቃው መድሎ እና ማግለል ነውና፡፡

ልክ እንደዚያው ሁሉ፣ የሀገረ-ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውንም ሁለንተናዊ ተግዳሮት ይኸው ይመስለኛል፡- መድሎ እና ማግለል፡፡ ሀገሪቷን በመምራት ላይ የሚገኘው መንግስት የሚከተለው የሚከተለው የፖለቲካ መርህ አግላይና አድሎአዊ ስለመሆኑ ለመናገር ብዙም መባከን አያስፈልግም፡፡ ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነው ጉዳይ ብቻውን በቂ አስረጅ ነውና፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ቢሆኑ ከዚህ ሁነት የራቁ አይደሉም፡፡ የተቃውሞ መሰረታቸውንና የትግል ስልታቸውን የቀየሱት በአድሎአዊና በአግላይነት መሰረት ላይ ነው፡፡ የሀገሪቱ ጋዜጠኞችም ሆኑ፣ ሌላ ሌላውም እንደዚያው ናቸው፡፡

እንዲያ ከሆነ ዘንዳ፣ ላለንበትና ለምንገኝበት ሁኔታ (ሀገሪቷም ጭምር) ተጠያቂዎች ሁላችንም ነን ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ስርዝ ድልዝ የሌለው እውነት ነው፡፡ እንዴት!? ላስረዳ፡፡ ከዛ በፊት ግን መድሎ ማለት ምን ማለት ነው!?ብለን እንነሳ፡፡

በ1951 ዓ.ም ለሕትመት የበቃው "ከሣቴ ብርሃን ተሠማ" የተሰኘው የአማርኛ በአማርኛ መዝገበ ቃላት "መድሎ" የሚለውን ቃል በሚከተለው መልኩ ፍቺ ይሰጠዋል፡- (1) ከሁለቱ ለአንዱ ለሚወደው አደላ፤ ልቡን ሰጠ፤ ሀሳቡን አበለጠ፡፡ (2) በፍቅርም ሆነ ጉቦ በመቀበል ለአንደኛው ወገን ማድላት፤ የሌላውን ወገን ማቃለል… ወዘተ ሲል ነው የሚፈታው፡፡

እኔ "የሌላውን ወገን ማቃለል" የሚለውን ፍቺ ነው ለፅሁፌ አግባብነት የመረጥኩትና አፅንኦት የምሰጥበት፡፡ እዚህ ላይ ታዲያ፣ መንግስት (ገዢው ፓርቲ) የአንዱን ወገን ይቅርታ ተቀብሎ፣ "የሌላውን ወገን ማቃለሉ"ን ነው ልብ እንድትሉልኝ የምፈልገው፡፡ ሆኖም ግን የእኔ ዕይታ በተለይ የሚያነጣጥረው ወደ ሌሎቻችን ነው፡- ወደ ሁላችንም፡፡ እኛስ!? እኔ፣ አንተ፣ እሱ፣ እሷ፣ እነርሱ፣ እሳቸው፣ እርስዎ (በአጠቃላይ ይህንን ፅሁፍ በማንበብ ላይ ያላችሁ ሁሉ) የሌላውን ወገን ህይወት፣ የሌላውን ወገን መስዋዕትነት፣ የሌላውን ወገን ትግልና ታጋይነት… ወዘተ አላቃለልንም ወይ? ነው ጥያቄው፡፡

ካለምንም መተፋፈር፣ ካለምንም መደባበቅ፣ ካለምንም ይሉኝታ እንነጋገር ከተባለ መልሱ አንድ እና አንድ ነው የሚሆነው፡፡ አቃልለናል!! ለዚህ ደፋር ነቀፌታዬ አብነት አድርጌ የማቀርበው፣ ይቅርታ ጠይቀው ከተነፈጉት እስረኞች እስረኞች መሀል አንዱን ነው፡- የተረሣውን ጋዜጠኛ፡፡

## <u>ማነው የተረሣው!?</u>

መንግሥት "ፀረ-ሽብር" በሚል ያረቀቀውን ሕግ በይፋ ካፀደቀ በኋላ፣ ከሁሉ አስቀድሞ የክስ ለበቁን የሰነዘረበት ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ እሱ ነው፡፡ በዕለተ ሰንበት ዕሁድ ሰኔ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ነበር በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ያዋለው፡፡ የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ (ነፍሷን ይማርና) ም/አዘጋጅ የነበረው ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ በድንገት ተጠርጥሮ መያዝ እኔን ጨምሮ የዝግጅት ክፍሉን ባልደረቦች በሙሉ ያስደነገጠ ዜና ነበር፡፡ በወቅቱ (በበነጋታው) ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ቁጥጥር ሥር የዋለበት ምክንያት እንዲገለፅላቸው ፖሊስን የጠየቁት "የአውራምባ ልጆች" ያገኙት ምላሽ ድፍን ያለ ነበር፡ - "የታሰረው ከሙያው ጋር በተያያዘ አይደለም" የሚል፡፡

የፖሊስ ምላሽ ይህ ቢሆንም፣ በ48 ሰዓት ልዩነት ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም የፍትህ ጋዜጣ አምደኛ የነበረችው ርዕዮት ዓለሙም በቁጥጥር ሥር ዋለች፡፡ ከውብሸት ታዬ ጋር በአንድ ፋይል ተዳብለው "የሽብርተኝነት ክስ" ተመሰረተባቸው፡፡ እናም ጥፋተኞች ተብለው የ14 ዓመት እስራት ተፈረደባቸው፡፡ (የርዕዮት ፍርድ በይግባኝ ወደ 5 ዓመት ዝቅ ማለቱን ልብ ይሏል) ከወራቶች በኋላ ደግሞ ይኸው የሽብርተኝነት ክስ "ዕጣ" ለጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ደረሰው፡፡ በአውራምባው ውብሸት ታዬ የተሟሸው ጋዜጠኞችን በሽብርተኝነት የመክሰስ ጉድ፣ እነሆ እስካሁን ጉድ እንዳሰኘን አለን፡ ፡ ለጉድ የጎለተን!!

የሆነ ሆኖ ከጋዜጠኞች ሁሉ አስቀድሞ በሽብርተኝነት የተከሰሰው ውብሸት ታዬ ነው፡፡ ከሁሉም በፊት ወደ እስርቤት የተወረወረውም እሱ ነው፡፡ ከተፈረደባቸውም አንዱ እሱ ነው፡፡ እንደተፈረደበት ካለምንም ማቅማማት መንግሥት ይቅርታ ያደርግለት ዘንድ ይቅርታ የጠየቀውም ጋዜጠኛ እሱ ነው፡፡ ይቅርታ የተነፈገው፣ ወይም ይቅርታው የተቃለለበትም

እሱዉ ነው፡፡ እንደው በጥቅሉ፤ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ በሁሉም ነገር በሁላችንም የተረሣ እስረኛ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ውብሸት የተረሳው በመንግሥት ብቻ አይደለም፡- በሁላችንም እንጂ፡፡

ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች፣ የጋዜጠኞች ማህበራት፣ በሃገር ውስጥም ከሀገር ውጪ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ግለሰብ የመብት መከበር አቀንቃኞች…ወዘተ ሁሉ የታሰሩ ጋዜጠኞች እንዲፈቱ ሲጠይቁ የውብሸትን ሥም የሚጠቅሱት በአለፍ አገደም ነው፤ ወይም አይጠቅሱም፡፡ ለምን እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር ባልችልም፣ የውብሸትን ጋዜጠኝነት ከነጭራሹ የዘነጉት ይመስለኛል፡፡ የሆነውና እየሆነ ያለውን ነገር የሰውነት ክብሩን፣ ሙያውንና ተስፋውን ጭምር የሚያደበዝዝ መሆኑ ከፉኛ ያሳስበኛል፡፡ ስለእሱ ግዴለሽነታቸው ይታሰበኝ ይዟል፡፡ ይህ ሁኔታ ታዲያ በርናንድ ሾ በአንድ ወቅት "ሀጢያት ነው" ሲል የተናገረውን ነው ያስታወሰኝ፡፡

"ከሁሉም የከፋው ሐጢያት ለመሰል ሰብዓዊ ፍጡራኖች ግዴለሽ መሆናችን ነው፤ ይህም የኢ-ሰብዓዊነት አይነተኛ መገለጫ ነዉ" ነበር ያለው፡- በርናንድ ሾ፡፡ አዎ! በእርግጥም ሥለ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ግዴለሽ ሆነናል፡፡ እየከፈለ ያለውን መስዋዕትነት አቃልለናል፡፡ በየትኛውም ሁኔታ ሥሙን እንኳ ከማንሳት ተቆጥበናል፡፡ በዚህ "ያልታሰበበት" ተግባራችን የእስረኝነት ተስፋውን ጭምር ያደበዘዝንበት መስሎ ይሰማኛል፡፡ ውብሸት ከታሰረ ጀምሮ ያለፉትን አንድ ዓመት ከ4 ወራት የሆነውንና እየሆነ ያለውን በጥሞና ስመዝነው፣ ከጋዜጠኞች መሀል አንዱን ብቻ ለይተን ሥሙንና ግብሩን ከፍ የምናደርግበት፣ የሌላውን ሥምና ግብር የምናቃልልበት ምክንያት ግራ ያጋባኛል፡፡ እነሆ ውብሸትን የማስታውሰው በዚህ ስሜት ውስጥ ሆኜ ነው፡፡

## <u>የተረሣውን ሳስታውስ</u>

ከአራት ዓመት በፊት ነው ከውብሸት ጋር የተዋወቅንበት አጋጣሚ የተፈጠረው፡፡ በጣም በቅርበት ለመተዋወቅ የበቃነው የአውራምባ ታይምስ ዝግጅት ክፍል ባልደረባ ከሆንኩ በኋላ ነው፡፡ በአውራምባ ጋዜጣ አብሮነታችን ወቅት ውብሸትን በተለየ መልኩ የማስታውሰው ቢሮ ውስጥ በምንገናኝበት ጊዜ ሁሉ እሱ ብቻ አዘውትሮ ከሚጠቀምባት ኮምፒውተር ጋር ነው፡፡ ይህቺ ኮምፒውተር በሌሎቻችን የአውራምባ ባልደረቦች የምትወደድ አይደለችም፡፡ ምክንያቱም እጅጉን የታወከች ናት፡፡ ውብሸት ግን በትዕግስት ይጠቀምባታል፡፡ እናም ሥራ ከመጀመሩ በፊት፣ ወይም በሥራው መሀል የኮምፒውተሯን ስክሪን ሲቨር በሕፃን ልጁ የተለያዩ ፎቶዎች ሲለዋውጥ ነው የማስተውለው፡፡

ሕፃን ልጁ ፍትህ ውብሸት አንዴ ኮፍያ፣ አንዴ መነፅር አድርጎ፣ እየሮጠ፣ ወይ ደግሞ ቁጭ ብሎ ወዘተ ያነሳውን ፎቶ በስክሪን ሲቨርነት እየለዋወጠ በተመስጦ ያየዋል፡፡ ፍትሕ የሚል ሥም ላወጣለት ልጁ የነበረው ፍቅር ይህ ነው አይባልም፡፡ ስለ ፍትህ አውርቶ፣ ስለ ፍትህ አልሞ የሚጠግብ አይመስልም፡፡ ከሥራ በኋላ እንደሌሎቻችን ለመዝናናት ብሎ አያመሽም፡፡ መሸት ሲል ልጄ ይጠብቀኛል ብሎ ወደቤቱ ይበራል፡፡ አንድ ቀን "ያንተ ደግሞ በዛ" ብዬ ልተቸው ስሞክር የሰጠኝ መልስ እስካሁን ድረስ ይገርመኛል፡፡ "የሕፃን ልጅ የአንገት ስር ሽታ ከሽቶ የላቀ መአዛ እንዳለው ብነግርህ ላንተ አይገባህም" ነበር ያለኝ፡፡

ውብሸት በሽብርተኝነት ተጠርጥሮ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር በዋለ ሰሞን ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ለንባብ ባበቃው አንድ መጣጥፍ ዋዘኛ ግን ደግሞ መረር ያለ "ቅድሚያ የደመወዝ ብድር ይሰጠኝ" ማመልከቻ አቅርቦ እንደነበር ያወሳው ትዝ ይለኛል፡፡ የውብሸት ማመልከቻ ዋዘኛነቱ "ልጄ ብርቱካን ሚደቅሳን ሆነብኝ" የሚል ይዘት ያለው መሆኑ ነው፡፡ ተከራይቶ የሚኖርበት ቤት አፋፍ ላይ የሚገኝ በመሆኑ እንደእስረኛ ልጁ ላይ በር ለመዝጋት እንደተገደደ በማመልከቻው ማተቱ ነው መራርነቱ፡፡ እናም የተሻለ ቤት ለመከራየት የሚያስችለው፣ ከደመወዙ የሚቆረጥ የቅድሚያ ብድር እንዲሰጠው በመጠየቅ ነው ማመልከቻውን ያሳረገው፡፡

ዛሬ ላይ ሆኜ ይህንን የውብሸት ማመልከቻ ሳጤነው ምፀታዊነቱ ጎልቶ ይታሰበኛል፡፡ የሁለት ዓመት ልጅን ፍትህን "ከእስረኝነት ኑሮ" ለማላቀቅ ይናፍቅ የነበረው ውብሸት ራሱ፣ በጥቂት ወራት ልዩነት እስረኛ መሆኑ ጥልቅ ምፀት

ይሆንብኛል፡፡ ሕፃን ልጁ ፍትህ፣ አባቱን በየሳምንቱ ስለ ፍትህ ሊጠይቀው ሲጠይቀው በዓይነ ህሊናዬ እየታየኝ አንዳች የሕመም ስሜት ይጓጉጠኛል፡፡

ከሁሉም በላይ የሚያሳምመው ግን፣ ውብሸት በሁላችንም የተረሣ እና የተዘነጋ መሆኑ ነው፡፡ የተሻለ ሕይወት እንመኛለን የምንል/የሚሉ፣ የተሻለ ነፃነት እንዲሰፍን እንመኛለን የምንል፣ የተሻለ ራዕይ አለን ለዚህም እንታገላለን የምንል/የሚሉ …ወዘተ ሁሉ፣ ስለ እሱ አፋችንን መዝጋታችን ያሳፍራል፡፡ ካላፈርንም ልናፍርና ሊያፍሩ ይገባል፡፡

በጋዜጣነቱ የከተበልንን ሐቅ እየነቀስን በአደባባይ ባንዘክርው፣ ስለተወልን ስራዎቹ ባንሸልመውና ባናሸልመው፣ ባለበት ቦታ እንዲበረታ በአካል ተገኝተን አይዞን ባንለው እንኳ፣ ስሙን በወጉ ለማስታወስ አለመሞከር ያስተዛዝባል፡፡ ከዚህ በላይ መድሎና ማግለል አለ እንዴ!?ያሰኛል፡፡ አዎ ያሰኛል! መድሎ እና ማግለል ይቁም!!

## የውብሸት ይቅርታ

ውብሸት የ14 ዓመት እስራት እንደተፈረደበት ይግባኝ የማለት ዕድል ነበረው፡፡ እሱ ግን ይቅርታ መጠየቅን ነው የመረጠው፡፡ እንደ እኔ እምነት ከይግባኝ ይልቅ ይቅርታ መጠየቅን የመረጠው ለልጁ ብሎ ይመስለኛል፡፡ ልጁ ለበርካታ አመታት ካለአባት ፍቅር እንዳያድግ በመሻት ይመስለኛል፡፡ በአባት ፍቅር እጦት ህሊናው እንዳይጠለሽ፣ የእናቱ እንግልትና መንከራተት እያየ እንዳይሰቃይ ያለው ፅኑ ፍላጎት ያስገደደው ይመስለኛል፡፡ እንጂ ይግባኝ ቢጠይቅ ረዥሙን የእስር ቤት ቆይታ ቢያንስ በእኩሌታው ማሳጠር ይችል ነበር፡፡ ሆኖም በፍጥነት ከልጁ ጋር የመገናኘት ጉጉት ምኞቱን አጓጉል አድርጎበታል ብዬ አምናለው፡፡ እናቶቻችን እንዲህ እንደውብሸት ያለ ሁኔታ ሲገጥማቸው፣ ነገር ሁሉ ተስፋ ከሚያደርጉት ወይም እንዲሆንላቸው ከሚሹት ውጪ ሲሆንባቸው መሰለኝ "ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ"ን የሚተርቱት፡ ፡

የውብሸት ግን ያለመታደል ነው ብዬ አላምንም፤ አይደለምም፡፡ ሆን ተብሎ የመረሳት፣ ሆነ ተብሎ የመተው የአድሎአዊነትና የአግላይነታችን ምስጢር መገለጥ እንጂ፡፡ ለዚህም አባባሌ ምክንያት አለኝ፡፡  ካለእኔ ታማኝ የዜና ምንጭ የለም የሚለው የETSAT ፊትአውራሪና የቀድሞው የ2 ወር አለቃዬ ፋሲል የኔ አለም ከሁለት ቀን በፊት ስለውብሸት ለጠየቁት የፌስቡክ ጓደኞቹ የሰጣቸው ምላሽ "ተፈቷል" የሚል ነው፡፡ አንድ ለእናቱና ለኢትዮጵያውያን ሐቀኛ የዜና ምንጭ ነኝ የሚለው ኢሳት ዋና ጋዜጠኛ  መረጃ ይህ ከሆነ ውብሸት ሆን ተብሎ ነው የተረሳው፤ ወይም እንዲረሳ የተፈለገው ማለት ያስደፍራል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ሁላችንም ራሳችንን፣ ፍላጎታችንን እና ተግባራችንን እንፈትሽ ዘንድ ግድ የሚል ይመስለኛል፡፡ የሰብዓዊ መብት ተሚጋቾች፣ የተሻለ ራዕይ አለን ባዮች፣ ዓለም አቀፍ የሙያ ማህበራትም ሆኑ ለለውጥ እንታገላለን የፖለቲካ ድርጅቶች …ወዘተ ሁሉ አንዱን ከፍ፣ ሌላውን አቃልለው የሚያዩበትን መስፈርት ሊመረምሩ፣ መመዘኛቸውን በእኩልነት ሊቃኙና ሊመረምሩ እንደሚገባ የሚጠቁም ይመስለኛል፡፡ በዚህም የተነሳ ደግሜ ደጋግሜ ለማለት የምፈልገው የሚከተለውን ብቻ ነው፡- መድሎ እና ማግለል ይቁም!! አዎ ይቁም!! ይኸው ነው፡፡ አበቃሁ!!